**የተከበራችሁና የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን !**

**ጥሪ የተደረገላችሁ የበዓሉ ተሳታፊዎች !**

**ክቡራትና ክቡራን !**

ከሁሉ በማስቀደም እንኳን ለ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓልና የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የፀደቀበት 20ኛው ዓመት አደረሰን እያልኩ የተሰማኝን ታላቅ ክብርና ደስታ በራሴና በኢፌዲሪ መንግሥት ስም ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

የዘንድሮው 9ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን "በሕገ መንግስታችን የደመቀ ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ቃል የተከበረው በቤንሻንጉል፣ ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና ሕዝብ አስተናጋጅነት ሲሆን በአሉ የኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ በሚገነባበት ክልል፣ ሕገ መንግሥታችን የፀደቀበት 20ኛ ዓመት 5ኛው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ለማካሄድ ዝግጅት በተጀመረበት እና የመጀመሪያው የእትእ በአጥጋቢ ሁኔታ ተከናውኖ 2ኛው የእትእ ዝግጅት ዋዜማ ላይ መሆኑ ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡

የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በሃገራችን ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማስፈን ፈርጀ ብዙና ምላአተ ሕዝቡን ያሳተፈና በሕዝብ ንቅናቄ ላይ የተመሠረተ እንቅስቃሴ

ተካሂዷል። የህብረተሰቡን ኑሮ በየደረጃው ያሻሻሉ ጉልህ ውጤቶችም ተመዝግበዋል።

መንግሥት የሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመፈተሽ ለሃገራችን ተስማሚ የሆኑ ሃገር በቀል ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች በመንደፍ፣ ይህንን ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት በመገንባት፣ የተለያዩ ሕገ መንግሥቱን ጨምሮ ሕጐች በማውጣት፣ የሃገራችን እድገት ሰፊ መሠረት ያለው ሕዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆንና ፍትሐዊና ሚዛናዊ ተጠቃሚነት እንዲኖር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ባለፉት 12 ዓመት ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት በማስመዝገብ በገጠርና በከተማ በምእተ አመቱ የልማት ግቦች በተቀመጠው መሠረት ድህነት በግማሽ እንዲቀንስ ተደርጓል። በማህበራዊ ልማትም በትምህርትና በጤና ዘርፎች የዓለምአቀፍ እውቅና የተቸራቸው ውጤቶች ተገኝተዋል። ብዙዎች ታዳጊ አገሮች የኢትዮጵያውያንን ምርጥ ተሞክሮ ለመውሰድ የቻሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በከተማም የልማትና መልካም አስተዳደር ስትራቴጂ ተነድፎ በከተማ የሚታየውን ሥራ አጥነት ለመቀነስ፣ የቤቶች እጥረትን በየደረጃው ለመቅረፍ፣ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ለማፋጠን ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው ተግባራት ተከናውነዋል።

በሀገራችን እስካሁን የተገኘው ድልና ስኬት መሠረታዊ የግለሰብና የቡድን መብቶች በህገ-መንግስቱ የተከበሩ ስለሆኑና ሁሉም እኩል እድል ተፈጥሮ፣ ፖቴንሻሉን በሙሉ አሟጦ እንዲጠቀም በተፈጠረ ምቹ የፖለቲካል ኢኮኖሚ

መሆኑ አያጠያይቅም። የሕገ መንግሥቱና የሕገ መንግሥታዊ ሥርአት ትርጉም መታየት ያለበት ከዚህ መሠረታዊ ጉዳይ አንፃር ነው።

## ክቡራትና ክቡራን

ሕገ መንግሥቱ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ብቻ ሳይሆን በጋራ ሆነው በመፈቃቀድ፣ በመከባበርና በዲሞክራሲያዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህብረሰብ ለመፍጠር መደላደልን ፈጥሯል። ለብዙሃነት ሕገመንግሥታችን እውቅና የሰጠው አንዳንድ ፀረ ሕዝቦች እንደሚሉት ማህበረሰቦችን ለመከፋፈል ሳይሆን ለአንድነታችን ጠንቅ የነበሩ የተዛቡ ግንኙነቶች በማስወገድ ያለማንም፣ ያለምንም ጫና የሚገነባ አንድነት ፋይዳ በማመን ነው። ለባህል፣ ለማንነት፣ ለእምነት ብዙሃነት እውቅና፣ እኩልነትና ሕገ መንሥታዊ ዋስትና መስጠት አንድነታችን ጽኑ መሠረት ላይ የሚያቆመው ስለሆነም ጭምር ነው። ብዙሃነታችን የነበረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር ውበታችንና ፀጋችን እንጂ በሕዝባችን ላይ የተጫነ እዳ ወይም እርግማን አይደለም። ይህን ነባራዊ ሃቅ በመካድ ሳይሆን በማቀፍ ነው እድገትና ወደፊት መራመድ የሚቻለው። እየተመዘገበ ያለው ውጤት ይህ ምቹ ሁኔታ ስለተፈጠረ ነው። ለዚህ ሌላ ማሳያ ሳያስፈልግ ከ24 ዓመታት በፊት የነበረውን የራሳችን ታሪክ ቆም ብሎ ማሰብ በቂ ነው። ሕዝቦችን ማንነታቸው በመካድ፣ ባህላቸውን በመናቅ፣ ቋንቋቸውን ዝቅ በማድረግ፣ መብታቸውንና ክብራቸውን በመንፈግ

በኃይል በመጫን አንድ ማድረግ አይቻልም፡፡ ሕዝቦች አንድ መሆን የሚችሉት በገዛ ፈቃዳቸውና በመከባበር ብቻ ነው፡፡

## ውድ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

ሃገራችን ዛሬ በውስጧ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ሰላምና መረጋገት እንዲፈጠር ያለሳለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ የዚህ መነሻና መዳረሻው ብሔራዊ ጥቅማችን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በውስጥ ሰላምና ልማት ባይኖር የሚታሰብ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር በጐረቤቶቻችን ያለውን ግጭትና ያለመረጋጋት በሰላም ለመፍታት በአደራዳሪነትና በሰላም ማስከበር ተግባር የበኩሏን ድርሻ እያበረከተች ትገኛለች፡፡

በዛሬ አለም አንድ ሃገር ብቻውን ለማደግ አይችልም፡፡ ከጐረቤቶች፣ ከዓለምአቀፍ አጋሮችና ተዋንያውያን ጋር በጋራ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ማድረግ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ሃገራችን ለልማቶቻችን፣ ለሰላማችንና ለምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ከሁሉም አጋሮቻችን ጋር ስትራቴጂያዊ አጋርነት በመመሥረት ላይ ያለነው፡፡

**ውድ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን**

**ክቡራትና ክቡራን**

ከላይ የተገለጹት ውጤቶች ያለተግዳሮትና ፈተና የተገኙ አይደሉም፡፡ አሁንም ያልተቀረፉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ የዴሞክራሲ ባህልና ተቋማት ወደሚፈለገው የጥንካሬ ደረጃ አለመድረሳቸው እና በአጠቃላይ ሃገራዊ የማስፀም አቅማችን በተሟላ መንገድ ያለመጐልበት፣ ለልማት ሥራችን የሚፈለገው ከፍተኛ የፋይናንስ ግኝት አሁን ያልተሻገርናቸው ፈተናዎች ናቸው፡፡ ይህ ለሀገራችን ብቻ የገጠመ ተደርጐ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ሁሉም ሃገራትና መንግሥታት በባህሪያቸውና በመጠናቸው ይለያዩ እንጂ ከተግዳሮቶችና ፈተናዎች ነፃ አይደሉም፣ ሊሆኑም አይችሉም፡፡

ችግሮቹና ፈተናዎቹ በውግዘትና በትችት ብቻ ሊወገዱ አይችሉም፡፡ ምንጫቸውን በሚገባ ለይተን አዋጭ የሆኑ አማራጭ መፍትሔዎችን በመፈለግ እንጂ፡፡ ስለሆነም በሃገራችን የተፈጠረውን ምቹ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የሃገራችን የድህነት፣ የረሃብ፣ የኋላቀርነትና የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ በአዲስ ታሪክ ለመቀየር የተጀመረው ህዳሴ አካል ለመሆን እድሉ አለን፡፡ ይህ ግን በእያንዳንዳችን ህሊናና ውሳኔ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም የታሪክ ተወቃሽ ወይንም ተወዳሽ የመሆን ምርጫ በእጃችን ነው፡፡

ዛሬ በዚህ በዓል የታደማችሁ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ቆም ብለን ሚዛናዊና ምክንያታዊ የሆነና በመርህ ላይ የተመሠረተ ተግባር ማከናወን ይኖርባችኋል። እያንዳንዱ የሕይወታችን ጉዞ ትርጉምና ዓላማ ያለው መሆን ይኖርበታል።

ውድ ወገኖቻችን፣

በቤኔሉክስ ሃገራት የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የጀመራችሁትን በጐ ተግባር በማጠናከር የሕዝባችንን ጥረት በመደገፍ የሕዳሴ ጉዞና ውጤት ስኬት አካል ለመሆን ከሚሲዮኑ ጋር በቅርበት መሥራት ተገቢ ይሆናል። ከዚህ ጉዞአችን ቢቻላቸው ለመነጠልና ጉዞውን ለማደናቀፍ የሚፍጨረጨሩ የጽንፈኞች አፍራሽ ድርጊት እንዲቆም የጋራ ድምጻችሁን ማሰማት ይኖርባችኋል። በህዝቡ ሳይመረጡ የሕዝቡን ሉአላዊ ምርጫ በመናቅ የሃገራችንና የሕዝባችንን ጥቅም ለመጉዳት የሚሯሯጡ አፍራሽ የፀረ-ልማት ኃይሎች የፀረ-ኢትዮጵያ ዘመቻ እንዲያቆሙ በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማረጋገጥ የተጀመረውን የትራንስፎርሜሽን ጉዞ ለማሳካት የበኩላችሁን ሚና እንድትጫወቱ በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

አመሠግናለሁ።